# ተናገር እምባዋ!!



Africans attempt to reach European Soil
(Reuters-July 10, 2008)

ፍልቅ፤ ፍልቅ ያልከው አምልጠህ ከአይኖቿ፣
ፊቷን ያለበሰከው ፈንድተህ ከአንጀቷ፣
ኮለል ያልክ በጉንጯ መንጭተህ ከልቧ፣
ዱብ ዱብ አይበቃም ተናገር እምባዋ!

መልእክትህ ብዙ ነው ተዝቆ የማያልቅ፣
አንድ ባንድ አስረዳ እንደሰው ሳትደብቅ።

ገና ስትጸነስ በናቷ ማህጸን፣
አባቷ ለፍትህ ገብሮ ህይወቱን፣
ንብረቱን ተገፎ እናት ለብሳ ጠኔን፣
እርሷም ምግብ አንሷት ቫይታሚን ፕሮቲን፣
ወደዚህ ምድር መጣች ሳለችና አጢሴን።

ፍልቅ፤ ፍልቅ ያልከው አምልጠህ ከአይኖቿ፣
ፊቷን ያለበሰከው ፈንድተህ ከአንጀቷ፣
ኮለል ያልክ በጉንጯ መንጭተህ ከልቧ፣
ዱብ ዱብ አይበቃም ተናገር እምባዋ!

አንገቷ ሳይጠና ሳይደርቅም እትብቷ፣
ተሰውረው ጠፉ ወንድምና እህቷ።

መዳህ ስትጀምር መሳብ መንቦራቸት፣
አሚካላና እሾህ ወለል ላይ ጠበቃት።

ዳዴ እየተባለች ለመራመድ ስትደርስ፣
በሽታና ችጋር ጠበቃት እንደ ውርስ።

ፍልቅ፤ ፍልቅ ያልከው አምልጠህ ከአይኖቿ፣
ፊቷን ያለበሰከው ፈንድተህ ከአንጀቷ፣
ኮለል ያልክ በጉንጯ መንጭተህ ከልቧ፣
ዱብ ዱብ አይበቃም ተናገር እምባዋ!

ማስተዋል ስትጀመር የአካባቢን ጉዳይ፣
አእምሮዋ ሲኳሽ አለምንም ስትቃኝ፣
ወንበር ላይ ቁጭ ብሎ አየች ነፍሰ-ገዳይ!

የአባቷ መረሸን ሳታይ ታያትና፣
የእት ወንድም መታፈን አሰቀቃትና፣
ሕጻናት በደዌ ሲረግፉ አየችና፣
መጪው ቀን ደቅድቆ ጨለመባትና፣
ለስደት ተነሳች ከእናት ጀርባ ሆና።

እግዚአብሔር ሲፈትን እስከመጨረሻው፣
መከራ ስቃዩን በእርሷ እንኳን አከፋው፣
መርከቡን ጀልባውን አንሸራታት አለው።

ተራራው አድባሯ ወንዟ ካባረራት፣
ባህር ውቂያኖሱ ሊያሰምጥ ከከጀላት፣
የባእድ አገር ምድር አልቀበል ካላት፤
ለዚች ጮርቃ ፍጡር ምንድነው እሚሻላት?

ፍልቅ፤ ፍልቅ ያልከው አምልጠህ ከአይኖቿ፣
ፊቷን ያለበሰከው ፈንድተህ ከአንጀቷ፣
ኮለል ያልክ በጉንጯ መንጭተህ ከልቧ፣
ዱብ ዱብ አይበቃም ተናገር እምባዋ!

በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)
ሐምሌ ሁለት ሺህ ዓ.ም.